# የንብ ማነብ በዘላቂነት ኑሮን ያሻሽላል!

## ለዚህም አስር ምክንያቶች አሉ፤



### 1. እጽዋትን ያዳቅላሉ

ንቦች የሚያብቡ እጽዋትን እያዳቀሉ ጥሩ ምርት ያስገኛሉ፣ ይህ ተግባራቸው ለሰው ልጅ በምድር ላይ ለመኖር ወሳኝ ነው።



### 2. ጠቃሚ ምርቶችን ይሰጣሉ

ማር በሁሉም ማኅበረሰብ ከፍተኛ ከበሬታ የሚሰጠው በምግብነቱም ሆነ በመድኃኒትነቱ የሚታወቅ፣ ሰም ለጧፍ መስሪያና ሌሎች ብዙ ጥቅሞችን የሚሰጥ፣ የንብ ሙጫና ዲናም በዘመናዊ አሰራር ከንቦች የሚገኙ እና ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጡ ምርቶች ናቸው።



### 3. ብዙ ቦታ አይጠይቁም

ንቦች አበቦች ከሚገኙበት አካባቢ እየሄዱ ምግባቸውን ስለሚሰበስቡ የንብ ማነብ የእርሻ መሬትን አይሻማም፤ በትንሽ ቦታ ብዙ ኅብረ-ንቦችን በማስቀመጥ የተሻለ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል።



### 4. ወጪው አነስተኛ ነው

ንቦችን በማደን ማግኘት ይቻላል፣ ቀፎውና ሌሎች የማናቢያ መሳሪያዎች በአካባቢው በቀላሉ ከሚገኙ ቁሳቁስ መስራት ስለሚቻል በጣም አነስተኛ በሆነ ወጪ ሥራውን መጀመር ይቻላል።



### 5. የገቢ ምንጭ ነው

የተሻለ ገበያ ባለበት አካባቢ የንብ ማነብ ጥሩ የገቢ ምንጭን ይፈጥራል።



### 6. ዘላቂ ልማት

ንቦች በተፈጥሮ ሃብት ላይ ጉዳት ስለማያደርሱ ለደኖች መኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።



### 7. የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ

ንብ ማነብ ለልሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ የሥራ ዕድል ይፈጥራል።



### 8. አንጻራዊ ጥቅም

በቂ የተፈጠሮ ሃብትና ጤናማ ኅብረ-ንብ ባለበት አካባቢ የተፈጥሮ ማር ማምረትና ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ በተሻለ ዋጋ መሸጥ ይቻላል።



### 9. በአጭር ጊዜ ጥቅም ያስገኛል

የንብ ማነብ በቀላሉ የሚጀመርና በአጭር ጊዜ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችል ሥራ ነው።



### 10. ጾታና እድሜ አይወስነውም

የንብ ማነብ በሴቶች፣ በወጣቶችና በአረጋዊያን ጭምር ሊካሄድ የሚችል የሙያ መስክ ነው።

ይህ "የንብ ማነብ በዘላቂነት ኑሮን ያሻሽላል" የሚለው ፖስተር የተዘጋጀው በንብ ሃብት ልማት ዘርፍ የመረጃና የምክር አገልግሎት በሚሰጠውና የበጀት ድጋፍ በሚያደርገው **ንቦች ለልማት ኢትዮጵያ** በሚባል ድርጅት ነው። የንብ ማነብ ሥራ ተፈጥሮ ሃብትን ለመጠበቅ፣ የሥራ እድልን ለመፍጠርና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንደሚረዳ ንቦች ለልማት ኢትዮጵያ ያምናል።

ንቦች ለልማት ኢትዮጵያ
ፖ.ሣ.ቁ.786
ሞባይል: 0918761182
ኢ-ሜይል: tilahun_gebey@yahoo.com
ምዕራብ ጎጃም ዞን
ባህር ዳር